በአማራ ብሔራዊክልላዊመንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡-የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/1480/18

ቀን፡-25/12/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ገቢዎች ቢሮ
ባሕር ዳር

ጉዳዩ፦ **የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም መሠረት፣ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ፣ እንዲሁም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን ለፍትሕ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንደሚገባው ተደንግጓል።

በዚህ መሠረት የገቢዎች ቢሮ በቁጥር ገቢዎችም.ቢ/3.8/265 በቀን 27/11/2018 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የተሸከርካሪ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት ላይ ተመስርቶ ታክስ ማስከፈያ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 21/2015 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወንለት መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትሕ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 21/2015 ዓ.ም በመመርመር መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 170/2018 ዓ.ም ሆኖ በሥራ ላይ እንዲውል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ.....ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ገረመው እሸቱ

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት (ያለ አባሪ)
- ለፍትሓብሔርና/ሕግ ጉዳይ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትሕ ቢሮ

Tl.No ☎ 058 222 0794/793 /058 226 52 92 ✉ 995

መመሪያ ቁጥር 170/2018 ዓ/ም

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ቢሮ የተሸከርካሪ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት ላይ ተመስርቶ ታክስ ማስከፈያ የአፈጻጸም መመሪያ

በክልላችን በተሸከርካሪ ሽያጭ ላይ የሚስተዋለው ከመገበያያ ዋጋ በታች ግምት እየቀረበ መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ገቢ እያስቀረ ስለሆነ የተሸከርካሪዎችን ግብይት ወቅታዊ የገበያ ዋጋ በማጥናት ትክክለኛና ወቅታዊ የተሸከርካሪን ዋጋ መሠረት ያደረገ ክፍያ ለማስከፈል እንዲቻል፤

የንግድ ሥራው ሀብት የሆነ ተሸከርካሪ በሽያጭ ወይም በስጦታ በሚተላለፉበት ጊዜ ከተሸከርካሪው የመዝገብ ዋጋ በላይ በተገኘው ጥቅም ላይ በልዩነቱ ላይ ግብር የማይከፍሉ በመሆኑ ይህንን ክፍተት በማስተካከል ተገቢውን ግብር ማስከፈል በማስፈለጉ፤

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ቢሮ በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 3(6) እና በገቢ ግብር አዋጅ 240/2008 አንቀጽ 93(3) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የተሸከርካሪ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት ላይ ተመስርቶ ታክስ ማስከፈያ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 170/2018 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 እና የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው።

2/ "ደንብ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢ ግብር እና ታክስ አስተዳደር አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 162/2010 እና 163/2010 ነው።

3/ "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ቢሮ ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ መምሪያዎች፣ ጽ/ቤቶች እና የቀበሌ ማዕከላትን ይጨምራል።

4/ "የቢሮ ኃላፊ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ የመምሪያ፣ የጽ/ቤቶችና የቀበሌ ማዕከላት ኃላፊዎችን ይጨምራል።

5/ "ተሸከርካሪ" ማለት ሁለት እና ከሁለት ጎማ በላይ ያለው፣ በሞተር ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰራ እና ለህዝብ እና ለእቃ ማጓጓዣ አገልግሎት የሚውል ማለት ነው።

6/ "የንግድ ሥራ ሀብት" ማለት የንግድ ሥራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ውይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ ሀብት ነው።

7/ "የተሸከርካሪ ዋጋ" ማለት ተሸከርካሪው በሚሸጥበት ወቅት የነበረው ትክክለኛ ወቅታዊና የገበያ መሸጫ ዋጋ ጥናት ሲሆን በአጥኝ ኮሚቴዎች ተጠንቶ በግብር አወሳሰን፣ አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት የፀደቀ ዋጋ ነው።

8/ “ትክክለኛ የገበያ ዋጋ” ማለት የእቃው፣ የንብረቱ፣ የአገልግሎቱ ወይም የጥቅሙ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ነው።

9/ “ኮሚቴ” ማለት በየደረጃው በሚገኙ የገቢ ተቋማት ወቅታዊ የተሽከርካሪ መሸጫ ዋጋ ጥናት እንዲያጠና ኃላፊነት የተሰጠው ኮሚቴ ነው፣

10/ “ሠው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

11/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸ አነጋገር የሴትንም ጾታ ያጠቃልላል።

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ተሽከርካሪዎች መለያ ቁጥራቸው ኮድ 1፣ ኮድ 2 እና ኮድ 3 የንግድ ተሽከርካሪ በማስተላለፍ ጥቅም በሚያገኙ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

ተሽከርካሪ በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ታክስ ስለመክፈል

4. ግብር ስለሚከፈልበት ሁኔታ

በገቢ ግብር አዋጅ 240/2008 አንቀጽ 21 በተደነገገው መሠረት በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተው የንግድ ሥራ ተሽከርካሪን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ከንግድ ሥራ ተሽከርካሪው የመዝገብ ዋጋ በላይ የሆነው የንግድ ሥራ ተሽከርካሪው በሚተላለፍበት ጊዜ ከተላለፈው ሀብት የተገኘ ገቢ ግብር ይከፈልበታል።

5. <u>የታክስ ስሌት</u>

1/ በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት አንድ በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተው የንግድ ሥራ ተሽከርካሪ በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ከንግድ ሥራ ተሽከርካሪው የመዝገብ ዋጋ በላይ የሆነው የንግድ ሥራው ተሽከርካሪ በተላለፈበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ በልጦ የተገኘው መጠን በንግድ ሥራ ገቢው ውስጥ ተካቶ በዚህ መመሪያ መሠረት ታክስ ይከፈልበታል።

2/ ተሽከርካሪን በማስተላለፍ ከተገኘው ጠቅላላ ጥቅም ውስጥ በንግድ ሥራ ገቢ የሚካተተው እና በዚህ መመሪያ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ መጠን ቀጥሎ በተመለከተው ቀመር የሚሰላ ይሆናል።

ሠ= ሀ-ሐ

ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፡-

ሀ) ተሽከርካሪው የተሸጠበት ዋጋ

ለ) ተሽከርካሪው የተገኘበት/የተገዛበት ዋጋ

ሐ) የተሽከርካሪው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ

መ) የግሽበት ማስተካከያ

ሠ) ከተሽከርካሪ ሽያጭ የተገኘ ጠቅላላ ጥቅም ወይም ኪሳራ

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገቢን ለማስላት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

6. ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶችን ስለመክፈል

1/ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 አንቀጽ 4 መሠረት በተሽከርካሪ ወቅታዊ የመሸጫ ዋጋ ላይ 2% ተርን ኦቨር ታክስ ይከፈልበታል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ግብር ከፋዩ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆነ በተሽከርካሪ ወቅታዊ የመሸጫ ዋጋ ላይ 15% ይከፈልበታል፡፡

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 አፈጻጸም ታክስ የሚከፈልበት የተሽከርካሪ ዋጋ የሚባለው በኮሚቴው ተገምቶ ከፀደቀው ወይም በትራንስፖርት ባለስልጣን ተገምቶ ከተላከው ወይም በተዋዋዮች ከቀረበው ውል የተሻለው ወቅታዊ የመሸጫ ጠቅላላ ዋጋ ላይ ነው፡፡

7. የቴምብር ቀረጥ ስለመክፈል

1/ በአማራ ብሔራዊ ክልል የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 31/1991 አንቀጽ 3 መሠረት ለተሽከርካሪ ስም ማዛወሪያ ወይም ለንብረት ባለቤትነት ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት ይሆናል፡፡

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም የቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው በኮሚቴው ተገምቶ ከፀደቀው ወይም በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ተገምቶ ከተላከው ወይም በተዋዋዮች ከቀረበው ውል የተሻለው ወቅታዊ የመሸጫ ጠቅላላ ዋጋ ላይ 2% ይከፈልበታል፡፡

8. ተሽከርካሪ በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢን ለማስላት እና ተሽከርካሪ ሲተላለፍ ሊቀርብ ስለሚገባ ሰነድ

1/ ተሽከርካሪው በሚተላለፍበት ጊዜ ከንግድ ሥራ ሀብቱ ጋር አብሮ የሚተላለፍ ዝርዝር የመዝገብ ዋጋ በግልፅ መቅረብ አለበት።

2/ ግብር ከፋዩ የሚተላለፈውን ተሽከርካሪ የተገዛበትን ወይም የተገኘበትን ዝርዝር ዋጋ ለይቶ ማቅረብ ይኖርበታል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተገዛበትን ወይም የተገኘበት ዝርዝር ዋጋ ማቅረብ ካልቻለ ከትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ባለስልጣን ከሚልከው መረጃ ላይ የሚወሰድ ይሆናል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተሽከርካሪው የተገዛበትን ህጋዊ ሰነድ ወይም የተገመተ ተሽከርካሪው የተገዛበት ዋጋ ማቅረብ ካልቻለ ታክሱ ከጠቅላላ ሽያጭ ላይ ተመስርቶ እንዲሰላ የሚደረግ ይሆናል።

5/ የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ ለተሽከርካሪ የተደረገውን ወጪ የሚከተሉትን ማስረጃዎች በማቅረብ ማረጋገጥ አለበት።

ሀ) ለተሽከርካሪው የተደረገውን ወጪ እና የተገኘበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰነድ፣

ለ) ተሽከርካሪው ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ስለእርጅና በጠቅላላው ተቀናሽ የተደረገውን ገንዘብ የሚያስረዳ ሰነድ

6/ ግብር ከፋዩ ተሽከርካሪውን በማስተላለፍ ያገኘውን ገቢ አግባብነት ባለው ማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን፤ በቀረበው ማስረጃ መሠረት ታክሱ የሚሰላው ማስረጃው በቢሮው ተቀባይነት ሲያገኝ ነው።

7/ ለተሽከርካሪው ስለተደረገው ወጪ እና ተሽከርካሪውን በማስተላለፍ ስለተገኘው ገቢ በግብር ከፋዩ የቀረበው ማስረጃ በገቢዎች ቢሮ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በሚጠና የወቅቱ የገበያ ዋጋ መሠረት ተሽከርካሪውን በማስተላለፍ የተገኘው ጥቅም ይሰላል።

8/ የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ወይም እንዲይዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ተሽከርካሪው የተገኘበትን ዋጋ/ ተሽከርካሪው በተገኘበት ወቅት የነበረውን ዋጋ ከትራንስፖርት እና ሎጂስቲክ ባለስልጣን አስገምቶ እንዲያቀርብ ይደረጋል።

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት ግብር ከፋዩ ተሽከርካሪው በተገኘበት ወቅት የነበረውን ዋጋ ከትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን አስገምቶ ካላቀረበ ግብር ከፋዩ ወጪ እንደሌለው ተቆጥሮ ታክሱ የሚሰላ ይሆናል፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገቢን ለማስላት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

11/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 አፈጻጸም 'አግባብነት ያለው ማስረጃ' ማለት የጸደቀ ውል ሲሆን በውሉ ላይ የተጠቀሰው የመሸጫ ዋጋ ተቀባይነት የሚያገኘው ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

9. <u>የተሽከርካሪ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት መስፈርቶች እና የኮሚቴዎች አደረጃጀት</u>

1/ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት ለማጥናት መነሻ የሚሆን መሰፈርቶች የአገልግሎት ዘመን፣ የተመረተበት አገር ተመራጭነት፣ የተመረተበት ፋብሪካ ተመራጭነት፣ መኪናው የሚሰጠው አገልግሎት ተፈላጊነት፣ መነሻ ዋጋ ዲክለራሲዮን፣ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ እና የግሽበት ማስተካከያ ላይ በመመስረት የወቅቱ ገበያ ዋጋ የሚጠና ይሆናል፡፡

2/ ወቅታዊ የገበያ ጥናት የሚያጠኑ አካላትን በሚመለከት በክልሉ ገቢ አሰባሰብና ክትትል፣ በዞን እና በሪጆ ፖሊታንት በእያንዳንዳቸው መምሪያዎች የተመረጡ 3 ባለሙያዎች ይሆናል፡፡

3/ በክልል ፣በዞን እና በሪጆ ፖሊታንት ከተሞች የተደራጀው ኮሚቴ በየጊዜው የተሽከርካሪ ስመ ንብረት ዝውውር ጥያቄ ሲቀርብ የተሽከርካሪዎችን ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ የገበያ ጥናት ዳሰሳ በማድረግ የሚያጠና ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገቢ አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት ጥናቱን ፍትሃዊ ለማድረግ እንዲቻል በየሶስት ወሩ የእያንዳንዱን የተሽከርካሪ ሞዴል ጥናት ለዞን እና ለሪጆ-ፖሊታንት ከተሞች የሚልክ ይሆናል፣

5/ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት የሚያጠኑ 3 (ሶስት) አባላትን የያዘ የኮሚቴ አደረጃጀት ሲኖር ስብጥሩም በተመለከተ የሚከተሉትን ያካተተ ይሆናል፡፡

ሀ) የገቢ አሰባሰብና ክትትል ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ባለሙያ ፣

ለ) የገቢ አሰባሰብና ክትትል ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ባልተሟላባቸው የእቅድ ባለሙያ እና የግብር ትምህርት ባለሙያ፣

ሐ) የገበያ ዋጋ ጥናት ባለሙያ(ባለባቸው ከተሞች/ዞኖች) አባል ይሆናሉ፡፡

መ) የግብይት መረጃ አሰባሰብና ስርጭትና አጠቃቀም ባለሙያ(ባለባቸው ከተሞች/ዞኖች) አባል ይሆናሉ፣

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ባለሙያዎች የአባላት ብዛት ከሦስት እንዳይበልጥ ሆኖ የሚደራጅ ይሆናል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተቋቋመው ኮሚቴ አማካኝነት የተጠናውን ወቅታዊ የቀጠና ዋጋ በግብር አወሳሰን፣ አሰባሰብና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪው በማስቀረብ ማፅደቅ ይኖርባቸዋል፡፡

7/ ተሽከርካሪን በማስተላለፍ የተገኘው ጥቅም ለማስላት የወቅቱን የሻጭና የገዥ ውል፣ በከተማ/ በዞን መምሪያ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን የተጠና የመሸጫ ዋጋ እና ቢሮው ያጠናውን የወቅቱ የገበያ ዋጋ በማነፃፀር የተሻለውን የገንዘብ መጠን የወቅቱ የገቢያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

10. <u>ለባንክ ዕዳ መክፈያ ስለተያዘ ተሽከርካሪ</u>

1/ በዋስትና የያዙትን ተሽከርካሪ ለብድር ዕዳ ማስመለሻ በሚያውሉበት ወቅት ንብረቱ ሲሸጥ ሊከፈል የሚገባው ተሽከርካሪ በማስተላለፍ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር ተፈጻሚ የሚሆነው ከንብረቱ ሽያጭ የተገኘው ገቢ ባንኮች የሰጡትን የብድር ገንዘብ ከሸፈነ በኃላ ቀሪ ገንዘብ ካለ ብቻ ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባንኮች የቅድሚያ መብት የሚኖራቸው በታክስ አስተዳደር አዋጅ 241/2008 አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው ተሽከርካሪዎች ብድሩ ከመሰጠቱ በፊት ታክስ ከፋዩ የታክስ እዳ የሌለበት መሆኑ ከቢሮው ከእዳ ነፃ ማስረጃ ለባንኩ ተጽፎ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

3/ ባንኮች ጨረታ አውጥተው ገዥ በማጣታቸው በመነሻ ጨረታ ተሽከርካሪውን ሲረከቡ የተረከቡበት ዋጋ ባንኩ ከሚፈልገው ዕዳ በላይ ትርፍ ገንዘብ ካለ ለቢሮው አሳውቆ በትርፉ ጥቅም ላይ ተሽከርካሪዎችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ግብር ይከፈልበታል፡፡ ሌላም ከተበዳሪው የሚፈለግበት የታክስ ዕዳ ካለ ለታክስ እዳው እንዲውል ይደረጋል፡፡

4/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም ባንኮች በዋስትና የያዙትን ተሽከርካሪ ወይም በፍርድ ቤት በጨረታ የሚሸጥ ተሽከርካሪን በሚመለከት በጨረታው ወቅት አሸናፊ

የሆነው የገንዘብ መጠን የወቅቱ የገበያ ዋጋ በመሆኑ ሌሎች ማነፃፀሪያዎች ሳያስፈልጉ ተሽከርካሪውን በማስተላለፍ የተገኘ ጥቅም ለማስላት ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው ቢኖርም ፍርድ ቤቶች ለዕዳ ማካካሻ እንዲውል ውሳኔ የሚሰጧቸውን ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጥናት ጋር በማነፃፀር የተሻለውን በመውሰድ የሚከፈሉ ክፍያዎች ከተከፈሉ በኋላ ተሽከርካሪ በማስተላለፍ የተገኘ ጥቅም ለማስላት የሚያገለግል ይሆናል፡፡

11. <u>ተሽከርካሪ በስጦታ ስለማስተላለፍ</u>

1/ ተሽከርካሪ በስጦታ ሲተላለፍ ስጦታ ተቀባዩ ተሽከርካሪ በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ወይም ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተሽከርካሪውን በስጦታ የሚያስተላልፈው ሰው የሂሳብ መዝገብ የሚቀርብ ከሆነ በስጦታ ከተላለፈው ተሽከርካሪ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ላይ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ከተቀነሰ በኋላ በሚቀረው የገቢ መጠን ላይ ግብር ወይም ታክስ የሚሰላ ይሆናል፡፡

3/ ተሽከርካሪውን በስጦታ የሚያስተላልፈው ሰው የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ወይም እንዲይዝ ግዴታ የሌለበት ከሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

12. <u>ተሽከርካሪ በውርስ ስለማስተላለፍ</u>

ግብር የሚከፈልበት የንግድ ተሽከርካሪ በሕግ ለተፈቀደላቸው ወራሾች በውርስ ሲተላለፍ ተሽከርካሪውን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ላይ ግብር አይከፈልበትም፡፡

13. <u>ዕጣን ወይም ድርሻን ስለማስተላለፍ</u>

የሕብረት ሥራ ማኅበራት የማኅበሩን ተሽከርካሪ በማስተላለፍ በሚያገኙት ገቢ ላይ ግብር እንዲከፍሉ አይጠየቁም፡፡

14. የሽያጭ /የስጦታ/ የልውውጥ ውል መፍረስ

1/ ግብር የሚከፈልበት የንግድ ተሽከርካሪ ለመሸጥ/በስጦታ ለመስጠት/ለመለዋወጥ የተደረገው ውል ሲፈርስ ተሽከርካሪውን በማስተላልፍ ከሚገኝ ገቢ ላይ የተከፈለው ግብር ተመላሽ ይደረጋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ድንጋጌ ቢኖርም ግብር ከፋዩ የከፈለው ግብር ተመላሽ እንዲደረግለት ለቢሮው ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ግብሩ ከተከፈለ በኋላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሉ መፍረሱን በሚመለከተው መስሪያ ቤት ማረጋገጫ በ10 ቀናት ውስጥ ካላቀረበ በህጉ እንዲከፍል ግዴታ የተጣለበትን ግብር ይከፍላል፡፡

ክፍል ሦስት

የተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

15. ወቅታዊ የገበያ ዋጋ አጥኝ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

1/ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ አጥኝ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ) ስመ ንብረት ዝውውር የተጠየቀባቸውን ተሽከርካሪዎች ከግብር ከፋዮች ማህደር ወይም ግብር ከፋዩ ከሚቀርብባቸው ሰነዶችን በመውሰድ ታሪካቸውን፣ የተፈበረኩበትን ጊዜ፣ ሊብሬ፣ ሻንሲ ቁጥር፣ የግብር ክሊራንስ ሁኔታ፣ መነሻ ዋጋ (የተገዙበት) መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣

ለ) ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ተገምተው የመጡትን ትክክለኛ የሽያጭ ወቅታዊ ዋጋ የእርጅና ቅናሽ ሳይቀነስ መረጃ መያዝ፣

ሐ) ሁለቱ ተዋዋዮች ሻጭና ገዥ የተገበያዩበትን ዋጋ መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣

መ) የገበያ ዋጋ ጥናት ባለሙያዎች፣ የግብይት መረጃ አሰባሰብና አጠቃቀምና ስርጭት ባለሙያዎች፣ ከገቢ አሰባሰብና ክትትል ባለሙያዎች በተሽከርካሪ አይነት ወቅታዊ የተሽከርካሪ መረጃ መረጃ መቀበልና ማደራጀት፣

ሠ) ከመኪና ደላሎች፣ ከአስመጪዎች፣ ኢንሹራንስና ሌሎች አካላት ወቅታዊ የተሽከርካሪ መሸጫ ዋጋ የአገልግሎት ዘመን፣ የተመረተበት አገር ተመራጭነት፣

የተመረተበት ፋብሪካ ተመራጭነት፣ መኪናው የሚሰጠው አገልግሎት ተፈላጊነት፣ መነሻ ዋጋ ዲክለራሲዮን፣ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ እና የማሸበት ማስተካከያ ታሳቢ በማድረግ መረጃ መሰብሰብ፣

ረ) የሌሎች ተመሳሳይ ተሽከርካሪዎችን የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣

ሰ) ለስመ ንብረት ዝውውር የቀረቡ ተሽከርካሪዎች ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ዳሰሳ በማድረግ ገምቶ ለግብር አወ/አሰ/ክትትል ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪ ማስተላለፍ፣

2/ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የቢሮው እና የመምሪያዎች የግብር አወ/አሰ/ ክትትል ዋና የሥራ ሂደትና የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

ሀ) አጥኝ ኮሚቴው በትክክል ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን በቂ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ለ) ከኮሚቴው ተጠንቶ የቀረበውን የተሽከርካሪ ወቅታዊ መሸጫ ዋጋ በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ መቅረቡን ማረጋገጥ፣

ሐ) የቀረበውን የተሽከርካሪ መሸጫ ዋጋ በጋራ በመገምገም ማጽደቅና የሚፈለገውን የመንግሥት ገቢ ወስኖ በማስከፈል ለፍትህ አካላት ማስተላለፍ፣

መ) የተሽከርካሪዎች መሸጫ ዋጋ ግምት አንዱ ከሌላው ያላቸውን ፍትሃዊነት በትክክል ማረጋገጥ፣

3/ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የቢሮውና የመምሪያ ኃላፊዎች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

ሀ) ኮሚቴው በትክክል ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን መከታተል እና የሚያጋጥሙ ችግሮችን እየተከታተሉ መፍትሄ መስጠት፣

ለ) በሥራ ሂደት ደረጃ የተሽከርካሪ ግምቱ የመንግሥትን ጥቅም በማያስቀር መንገድ እየተፈፀመ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ) የተሽከርካሪ መሸጫ ዋጋ ግምት ፍትሃዊነቱን መረጋገጥ

መ) በኮሚቴው በኩል በዋጋ ጥናት ጋር ተያይዞ የሚያጋጥሙ የስነ ምግባር ችግሮች ሲያጋጥሙ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

ሠ) በየጊዜው የሚስተዋሉ ችግሮችን እየፈተሹ መመሪያዎችንና አሰራሮች ክለሳ እንዲደረግ ለቢሮው ግብዓት መስጠት፣

16. የትራንስፖርትና ሎጅስቲክ ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊነት

1/ የትራንስፖርትና ሎጀስትኪስ ባለስልጣን የተሸከርካሪውን ትክክለኛ መሸጫ ዋጋ ገምቶ በየደረጃው ለሚገኘው የቢሮው መዋቅር ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የገዥና ሻጭ የተሸከርካሪ ሽያጭ ውል የሚፀድቀው ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን እና ከቢሮው ትክክለኛ የተሸከርካሪው መሸጫ ዋጋ ተገምቶና ክፍያ ተከፍሎ ሲቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

3/ በየደረጃው የሚገኙ የገቢ ተቋማት ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ተገምቶ የቀረበውን፣ በተዋዋዮች መካከል የቀረበው የተሸከርካሪ መሸጫ ዋጋ እና በኮሚቴው የተጠናውን ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት በማነጻጸር የተሻለውን በመውሰድ ማስከፈል ይኖርበታል፡፡

4/ የንግድ ተሸከርካሪዎችን ከንግድ ሥራ ገቢ ግብር ለመሸሽ የተሸከርካሪ ኮዳቸውን ወደ ኮድ 2 የሚቀይሩ ግብር ከፋዮች በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን በሚወጣው መመሪያ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት የሚቀጡ ይሆናል፡፡

17. የፍትህ ቢሮ መምሪያ ጽ/ቤት ኃላፊነት

1/ የገዥና ሻጭ የተሸከርካሪ ሽያጭ ውል በፍትህ የሚፀድቀው ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን እና በቢሮው ትክክለኛ የተሸከርካሪው መሸጫ ዋጋ ተገምቶና ክፍያ ተከፍሎ ሲቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን ድንጋጌ በመተላለፍ የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግምት ውስጥ ሳይገባ በገዥ እና በሻጭ ውል ወይም በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ግምት ብቻ የተላለፈ ስመ ንብረት ዝውውር የመንግሥት ጥቅም ለማስከበር ሲባል ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

18. ከግብር ከፋዩ ወይም ከአገልግሎት ፈላጊዎች የሚጠበቁ ግዴታዎች

1/ ግብር ከፋዩ ወይም ሻጩ የተሸከርካሪውን ሊብሬ ኮፒ፣

2/ ግብር ከፋዩ ወይም ሻጩ የተሸከርካሪውን የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የታደሰ መንጃ ፈቃድ፣

3/ ግብር ከፋዩ ወይም ሻጩ ተሸከርካሪው ሌላ ቦታ ከሆነ ቁመናውን የሚያሳይ ከፊት፣ ከጎንና ከኋላው ሻንሲ ቁጥሩን በሚያሳይ መንገድ በቪዲዮ ቀርፆ፣

4/ ተሸከርካሪው የተላለፈው በስጦታ ከሆነ ውል ወይም ሻጭ እና ገዥ የተሻሻጡበትን ውልና ባንክ ገቢ የተደረገበትን ገንዘብ ዝውውር የተፈፀመበትን ደረሰኝ እና

5/ ግብር ከፋዩ ወይም ሻጩ ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ተገምቶ የቀረበ ትክክለኛ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19. ከቴምብር ቀረጥ እና ከንግድ ሥራ ግብር ነጻ ስለመሆን

1/ ከታክስ (ኮድ 1) እና ከንግድ (ኮድ 3) በስተቀር ሌሎች ተሽከርካሪዎችን በመሸጥ ወይም በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ሊከፈልበት አይችልም።

2/ በክልሉ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ተሽከርካሪ ስም ማዛወሪያ ወይም ለንብረት ባለቤትነት ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ የቴምብር ቀረጥ አይከፍሉም።

20. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ ይህ መመሪያ ከመጽናቱ በፊት ተሽከርካሪን በማስተላለፍ በተገኘ ጥቅም ላይ ግብር ስለመክፈል በእንጥልጥል ላይ ያሉ ወይም ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት የሚስተናገዱ ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተደነገገው ቢኖርም ተሽከርካሪን በማስተላለፍ በተገኘ ጥቅም ላይ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ተወጥተው የስም ለውጥ ሳይተላለፍ የቀሩ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ አይሸፈንም።

3/ የንግድ ትርፍ ግብር የማይመለከታቸው ኮድ 2፣ ኮድ 4፣ ከተቋቋሙበት ዓላማ ጋር በተያያዘ ኮድ 5 እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተሽከርካሪ ሽያጭ፣ በባልና ሚስት እና በቤተሰብ መካከል የሚደረግ የሀብት ክፍፍል፣ የተሽከርካሪ ውርስ፣ ግለሰቦች በተለያየ ምክንያት ከአሁን በፊት የነበራቸውን የስም ለውጥ ሲያደርጉ፤ የንግድ ድርጅቶች ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ሲዋህዱ፣ በካፒታል መዋጮ ተሽከርካሪዎች በሚተላለፉበት ወቅት፣ ግለሰቦች ተሽከርካሪዎቻቸውን ወደ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲተላለፍ በሚደረግ ስመ ንብረት ዝውውር ላይ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር አይከፈልበትም።

21. ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያዎች ወይም ሰርኩላሮች ወይም የተለመዱ አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

22. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ በቢሮ ኃላፊው ተፈርሞ ከወጣበት ከታህሳስ ቀን 2015 ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በገቢዎች ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ጸጋ ጥበቡ (ዶ/ር)

የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ